# የወያኔ ስብሰባ በቶሮንቶ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው፤

## የተቀዋሚው ወገን በአንድነት ድምጹን አሰማ

በሰሜን አሜሪካ ከተሞች የወያኔ ባለስልጣኖችና ካድሬዎች በጠሩት ስብስባ ሁሉ ቅሌትና ውርደታችውን እየተከናነቡ ባሉበት ጊዜ በቶሮንቶ ካናዳም ተመሳሳይ የውርደት ማቃቸውን ተከናንበው መዋላቸው ታውቋል።

እሑድ ኤፕሪል 10 ቀን 2011 ዓ/ም 89 Chestnut St. በሚገኘው በዩንቨርሲቲ ኦፍ ቶሮንቶ ኮንፈረንስ ማእከል በወያኔ ኤምባሲና ሆዳም ካድሬዎች የተጠራው ስብስባ ከቀኑ 7 ሰዓት ቢሆንም አንዳንዶቹ ከጠዋቱ 5 ሰዓት ጀምሮ እየተሽሎከለኩ ሲገቡ የታዩ ሲሆን ሰልፈኛው የሚጥለውን ዶፍ ዝናብ ከምንም ሳይቆጥር ከረፋዱ 5፡30 ጀምሮ በቦታው መገኘት የጀመረ ሲሆን በ12፡00 ሰዓት ላይ መፈክሮቹንና እያነገበና ሰንደቅ ዓላማውን እያውለበለ በመሰባሰብ ድምጹን ማሰማት ጀመረ።




ቆራጥ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነው መፈክራቸውን በማሰማት የወያኔ አጫፋሪዎች አይናቸውን ከተቃዋሚው ሰልፈኛ ከልለው እየተሸማቀቁ በውርደት ሲገቡ ማየት በእጅጉ የሚያሳፍር ሲሆን አንዳንዶቹም በሴኩሪቲ ሰዎች አናስገባም ተብለው መሄጃ አጥተው በሞባይል ስልካቸው ፊታቸውን ከልለው አፍረው ሲመለሱ ታይተዋል። አንዳንድ ሆዳቸው አምላካቸው የሆነባቸው ሀይማኖተኛ ይመስል የእስልምና ምልክት ኮፍያቸውን አድርገው ሲገቡ ለገጠማቸው ተቃውሞ በባህላችንና እጅግ አሳፋሪ የሆነ የብልግና ምልክት በእጅና በጣታቸው በማሳየት ብልግናና ጥጋባቸውን ሲያሳዩ አለቃቸው መለስ ዜናዊም ከጥቂት ዓመታት በፊት ዋሽንግተን ዲሲ ኤምባሲው ሲገባ ለተቃዋሚው ወገን በእጁ አጸያፊ የብልግና ምልክት ማሳየቱን እንደ ባህል መቁጠራቸውን ያሳያል።






ለስድስት ሰዓት ያህል ያለማቋረጥ መፈክር በማሰማት፣ የትግል መዝሙርና በመዘመር፣ መልእክት በማስተላለፍ አገራቸውን ለሆዳቸው ሸጠው የሚገቡትን በተቃውሞ ድምጽ በማሳፈር የቀጠለ ሲሆን የተቃውሞ ሰልፈኛው በሙሉ በአንድነት መቆማቸውን በማሳየት በጨዋነት መንፈስና በመከባበር የመጡበትና ዓላማ ከግቡ በማድረስ እጅግ በሚያስደስት ሁኔታ ህግና አክብረው ቆይተዋል።






የተቃውሞ ሰልፈኛው ከያዛቸው መፈክሮች መካከል፡መለስ ዜናው ለፍርድ ይቅረብ፣ መለስ ዜናው አገሩን የሸጠ ወንጀለኛ ነው! የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ አመጽ መገርሰሱ አይቀሬ ነው! የአርሶ አደሩ መሬት ለውጭ ከበርቴዎች መቸብቸቡ ይቁም! አገራችሁን ለሆዳችሁ አትሸጡ! የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ! ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንቆማለን! አገራችንን በጋራ እናድን! ሕዝብ እየተራበ የኢኮኖሚ እድገት የለም! የጎሳ ፌዴራሊዝም ጸረ- ዲሞክራ ነው!RECOGNIዘE THE OGADEN GENOCIDE! TPLF IS A SYMBOL OF ETHNIC DIVISION & POLITICAL APARTHEID! እና ሌሎችም በርካታ መፈክሮች ነበሩ።





ወያኔ ለ20 አመታት ሕዝቡን በመሳሪያና በጉልበት፣ በመከፋፈልና በማጋጨት፣ በመግደልና በማሰር፣ አገር በመቁረስና በመሸጥ፣ ዘር በማጥፋት ወንጀል ታሪክ ይቅር የማይለው ከፍተኛ ወንጀል የፈጸመ ሲሆን  ጥቂት ሆዳሞችና አጫፋሪዎችን በጥቅም በመያዝ ዛሬ እድገትና ልማት አመጣለሁ እያለ የሚለፍፈው የጥፋት እድሜውን ለማርዘም ስለሆነ፤ ለሆዳቸው ባደሩና የወያኔን አገዛዝ በደገፉ ሰዎች በሚካሄድ ማንኛውም የንግድ መስክ ላይ የኢኮኖሚ ማእቀብ እንዲደረግ ማሳሰቢያ ሲሰጥ ተቃዋሚው በሙሉ ያንን በመደገፍና የኢኮኖሚ ማእቀቡን ተግባራዊ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

እንዲሁም የካናዳን ሲሰተም በመጠቀም በጎን ደግሞ ከወያኔ ጋር እተሞዳሞዱ የሚነግዱትን በማጋለጥ በካናዳ መንግስት ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ አለብን ተብሏል። ከምሽቱ 12 ሰዓት ሲሆን የወያኔ አጫፋሪ በጓሮ በር እየሾለከ በመሄዱ ሰልፈኛውም በመጣበት ሁኔታ በሰላም ተመልሷል።












ተዳክሞ የነበረው የተቃዋሚው እንቅስቃሴ ተበራትቶ በጋራ ለመታገል መነሳቱ እሰየው ያሰባለና ተቃዋሚውን ጎራ በእጅጉ ያስደሰተ ሲሆን ተመሳሳይ የተቃውሞ ድምጽ እንደሚቀጥልም ሲነገር፣ በወያኔ ጎራ ብርክና ድንጋጤም እንደፈጠረ ታውቋል።

ቪቫ ቶሮንቶ !